PANORAMA # XXX

# የትዝብት አድማስ

ሰኔ 20 2000

## የትግላችን ግቡ የኢትዮጵያን ዘላቂ ጥቅም ማስጠበቅ ነው

የኢትዮጵያን ስም አንግበው የተደራጁ ፓርቲዎችና ሌሎች ድርጅቶች፥ ከሁሉ በፊት ሊገነዘቡት የሚገባ አንድ መሠረታዊ ጉዳይ አለ ብለን እናምናለን። በኢትዮጵያ ስም መደራጀትና መታገል ማለት፥ መብት ብቻ ሳይሆን፥ ግዴታም፥ ክብርም፥ መታደልም፥ ብሎም ከባድ ኃላፊነትም ማለት መሆኑንም ጭምር ነው። እንደ ግንባር ቀደሙ ትውልድና አኩሪ ታሪክም አስመዝግቦ እንዳለፈው ገዲም ሰማዕታት ዜጋ፥ ዛሬ በኢትዮጵያ ስምና ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅም እታገላለሁ የሚል ሁሉ፥ የዓላማው ማዕከል፥ የትግሉ አልፋና ኦሜጋ እንዲሁም የመጨረሻ ግቡ፥ የኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅምና የዜጎቿም ብሔራዊ ነፃነት መሆን አለበት። በዚህ አብይ መተከል ዙሪያ የማይካሄድ ትግል፥ የመጨረሻ ግቡን ሊመታ ቀርቶ፥ ደረቅ ወንዝ እንኳን መሻገር አይችልም ።

ከታሪክና ከትውልድ ብያኔ አኳያ ሲገመገም፥ አሁን ስለአለው የሀገራችን ሁለንተናዊ ሁኔታ፥ ሁሉም የየድርሻውን ባለመወጣቱና ወያኔን ባለማንበርከኩ፥ ብሎም የሀገሪቱን መከራ ባለማስወገዱ፥ የየበኩሉን ኃላፊነት መቀበል የግድ ሊሆን ነው። የወያኔ መሪዎች ድሮውንም ቢሆን አመጣጣቸው ለኢትዮጵያ ጥፋት ስለሆነ፥ በታሪክ ፍርድ ሸንጎ የሚቀርቡት በተለየ ምዕራፍ በመሆኑ፥ ለነርሱ የሚሰጠው ብያኔ የተለየ ይሆናል። ይህም በመሆኑ ዛሬ እኛ ማተኮር የሚገባን በኢትዮጵያ ስም፥ ስለ ኢትዮጵያ በሚታገሉት ኃይሎች ላይ ነው። ውሸት እንደ ዕውነት ተቆጥሮ፥ በዕውነት መቃብር ላይ ሀሰት ነግሶ፥ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መልክአ - ምድር ላይ አጥፊ ሚና በሚጫወትበት በአሁኑ ዘመን፥ ዕውነቱን ተናግረን፥ ዕቅጩን አሰምተን፥ ድክመታችንን አምነን፥ አቅማችንን አውቀን፥ የጋራ ኃላፊነትን ተቀብለን፥ መታገል ካልተቻለ፥ ነገር-ዓለሙ ሁሉ የእምቧይ ካብ ከመሆን አያልፍም። ያልታገሉት ትግል፥ እንደ ባቢሎን ግንብ ሆኖ ይቀራል።

“ተግባራችን ሁሉ ካልረገጠ ዕርካብ፥
ዓላማችን ከንቱ የዕምቧይ ካብ የዕምቧይ ካብ”
ብለው ነበር አንድ ኢትዮጵያዊ ስመጥር ደራሲ

በአሁኑ የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ያለውን ዕውነታ ስንመለከት፥ ለመካድ የማንችላቸው አራት ነገሮች እፊታችን ይደቀኑብናል።

1ኛ. የምዕራብያውያንን ጥቅም የሚያስጠብቅና የሀገራችንንም ብሄራዊ ጎላዊ በማጥፋት ላይ የሚገኝ አንድ ጠባብ ብሄረተኛ ቡድን በሥልጣን ላይ እስካሁን አለ። ምዕራብያኑም ለጥቅም አስጠባቂያቸው ለዚህ አጎብዳጅና

ተላላኪ ቡድን፥ ሁለንተናዊ ድጋፍ እየሰጡት ይገኛሉ፡፡ ዛሬ ከመላው የአፍሪካ ክፍለ አኅጉር ውስጥ፥ ከግብፅ ቀጥሎ ከፍተኛውን እርዳታ የሚያገኘው መለስና አጎብዳጅ ቡድኑ ነው፡፡ ይህም የልብ ልብ ሰጥቶት፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደ "ገል ቀጥቅጨ፥ እንደ ሰም አቅልጨ ለብዙ ዘመን እገዛለሁ" ብሎ ያምናል፡፡ የሀገራችን የጂኦ-ፖለቲካ ጠቀሜታ ከቁጥጥራቸው ሥር እስካለ ድረስም፥ ምዕራባውያኑ፥ አስፈላጊውን ሁሉ እርዳታና መመሪያ ከመስጠት አይቆጠቡም፡፡ ታዲያ ያም ሆኖ፥ በአንድ ነገር ግን በዕርግጠኝነት መናገር እንችላለን፡፡ በዓለም አቀፍ ግንኙነት ዘይቤና በሀገሮች መካከል ሊኖር በሚችለው የዲፕሎማሲ ዘማዊነት መሠረት፥ "ዘላቂ ወዳጅ ወይም ዘላቂ ጠላት ሳይሆን፥ ሊኖር የሚችለው፥ ዘላቂ ጥቅም ብቻ" መሆኑን ስለምናወቅ፥ የምዕራባውያን ድጋፍና ትብብር የሚለገስለት፥ የአገልግሎት ጠቀሜታው እስካለ ድረስ ብቻ ይሆናል፡፡ አገልግሎቱ ሲያከትምባቸውና ጠቀሜታው ሲወይብባቸው፥ መለስን እንደ አገዳ መጥጠው እንደሚተፉት ካለፈው ተመክሯቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡

ለኢራኑ ሻህ፥ ለዛየሩ ሞቡቱ፥ ለሩሜንያው ቻውቼስኩ፥ ለሶቭየቱ ሚካኤል ጎርባቾቭ፥ ያልሆኑ፥ ሕዝባዊ አመፅ ሲመጣ ፥ ምዕራብያውያን፥ ለመለስ ዜናዊ ይቆሙለታል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ መሰሪው መለስም ይህን ይስተዋል አንልም፡፡ ኢትዮጵያ በታሪኳ እንደነመለስ ዜናዊ የመሳሰሉ የሀገራቸውን ጥቅም ለባዕድ አሳልፈው የሰጡና ብሄራዊ ክብሯንም ያዋረዱ መሪዎች አጋጥሟት ስላልነበር፥ ይህ የታሪክ ሀፍረት ለነመለስ ዜናዊ ብቻ ሳይሆን፥ ለዚህ ትውልድም ጭምር እንዳይተርፍ ያሳስበናል፡፡ እነ አሉላ አባ ነጋን ያበቀለች የትግራይ ምድር፥ ከአንድ ምዕተ ዓመት በኋላ፥ እንደነመለስ ዜናዊ ዓይነቶቹን ሀገር ሻጭ ግለሰቦችን ማፍራቷ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ እየገረመው ይኖራል፡፡ ከሱዳን ጋር የሚያዋስነውን ሰፊና ለም የሀገራችንን የምዕራብ ግዛት ለሱዳን የሚያስረክብ ቡድን ኢትዮጵያዊ ነው ለማለት የሚያስቸግር ነው፡፡ ባይሆን ኢትዮጵያ አርጅታለች አንልም እንጅ፥ ለካስ "ሀገር ሲያረጅ ጃርት ያበቅላል" የሚባለው ይትብሃል፥ ዕውነት ኖሯል?

2ኛ. በሁለተኛ ደረጃ ሊወሳ የሚገባው የተቃዋሚው ጎራ ነው፡፡ <u>ኢትዮጵያንና ብሄራዊ ጥቅሟን</u> <u>ማዕከል ያደረገ አርድ አንቀጥቅጥ ትግል ማካሄድ እስካሁን አልተሳካለትም</u>፡፡ ከሁሉም በላይና በበለጠ ደግሞ፥ የኢትዮጵያ ስትራተጂያዊ ጥቅም ማለት፥ የሕዝቧ አንድነትና ኅብረት ማለት እንደሆነም በጭራሽ በሚገባ የተረዳ አይመስልም ፡፡ የተፋፋመ፥ ሁሉንም ትግል ማየት፥ አሁንም የሁሉም ኢትዮጵያዊ ህልምና ምኞት ሆኖ ቀርቷል፡፡ የተቃዋሚው ጎራ፥ በድቡሽት ላይ ጎጆ ለመቀለስ ከመጣር ይልቅ፥ መሠረተ ፅኑ፥ አግማሰ-ትልቅ፥ ራዕዩ-ጥልቅ፥ አዳራሹ ሰፊ፥ ሁሉን አቃፊ የሆነ ሀገር ለመገንባት የሚያስችለውን ቅድመ-ዝግጅትና ሂደት ማድረግ ነበረበት፡፡

ደርግ ሀገሪቱን ለበላዒ-ሰብ አጋልጧት ከሄደ ከ1983 ዓ ም ጀምሮ የተቃዋሚው ጎራ ኅብረት ለመፍጠር ያደረገው ሙከራ ሁሉ ለምን እንዳልተሳካለት እንኳን፥ ወደ ኋላ ዘወር ብሎ በመመልከት፥ ምክንያቱን ለማሰስ የሞከረ የለም፡፡ ለአለፉት አስራ ሰባት የውርደትና የጥቃት ዓመታት፥

*ስምንት የኅብረት ምሥረታ ጥረትና ሂደቶች ተደርገዋል፡፡ ኢዴኃቅ፥ ፓሪስ አንድና ፓሪስ ሁለት፥ አማራጭ ኃይሎች፥ኢተፖድኅ፥ ቅንጅትና ኢዴኃኅ ለማስረጀ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ስምንት ጥረቶች ቢደረጉም፥ የተጠበቀውን ውጤት ሊያስመዘግቡ አልቻሉም፡፡ የሚገርመው ደግሞ፥ ከእነኝህ ሙከራዎች ውስጥ አንዳንዶቹ፥ የተቃዋሚ ድርጅቶች ኅብረት ለመመስረት የተዘጋጀው ሰነድ የተፈረመበት ቀለም ከመድረቁ በፊት ይፈራርሳሉ፡፡ "ጨዋታው ፈረሰ ዳቦው ተቆረሰ" እየተባባለ ሁሉም በየፊናው ይሄዳል፡፡*

3) *የኢትዮጵያ ምሁራን ለሀገራቸው መቆርቆርና ለውጥም ለማምጣት እስካሁን ያደረጉት ጥረት የማይናቅ ለመሆኑ ሁሉም የሚስማማበት ይመስለናል፡፡ ይህ ሀቅ እንዳለ ሆኖ ግን፥ ምሁራኑ በተቃዋሚው ጎራ የትግል ሂደት የሚገባቸውን ሚና ለመጫወት ዕድል አግኝተዋል ለማለት ያስቸግራል፡፡ በተናጠልና አልፎ አልፎም በቡድን እየሆኑ ያደረጉት ጥረትና ድካም፥ ውለታ መላሽ በሆነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ አዎንታዊ ግንዛቤ እንዳተረፈ ማንም የሚያውቀው ይመስለናል፡፡ ምሁራን ከዚህ አልፈው ግን፥ ሰፊና ትልቅ መድረክ በማዘጋጀት፥ ለትግሉ ሂደትና መሳካት የሚረዳ ትምህርት በመስጠትና ተጽዕኖ በማሳደር ሊያደርጉት የሚገባቸውን ግዴታ ሁሉ ተወጥተውታል ለማለት የሚቻል አይመስለንም፡፡ <u>ይህንን ለማለት የምንደፍረው፥ የምሁራንን ሁለንተናዊ ድጋፍና አስተዋጽዖ የተነፈገው ትግል ስኬታማ እንደማይሆን ስለምንረዳ ነው፡፡ የምሁራኑ ሁለንተናዊ ተሳትፎ ከምንጊዜውም በበለጠ የሚያስፈልግበት ወቅት ቢኖር ዛሬ ነው</u>፡፡*

*እንግዲህ፥ ሀቁን እየተናገርን በመሸበት እንደር ከተባለ፥ የተቃዋሚው ድርጅቶች ጎራና የኢትዮጵያ ምሁራን አንድ አምሳል አንድ አካል ሆነው ሀገራቸውን ከጥፋት ለማዳን፥ ከሕዝብ ጋር ከተዋሀዱ ያመረቃና ቀጣይ ትብብር ካደረጉ ትግሉ በአጭር ጊዜ ግቡን እንደሚመታ አይጠረጠርም፡፡ የምሁራንን ድጋፍና ተሳትፎ ያልተጎናፀፈ ትግል የትም እንደማያደርስ ሁሉም ሊገነዘበው ይገባ ነበር፡፡ ምሁራኑ እራሳቸው ተባብረውና ተስማምተው፥ የበኩላቸውን የትግል አስተዋፅዖ ማድረጋቸው ደግሞ ሀገራዊ ግዴታና ተግባር ይመስለናል፡፡ ሰኔና ሰኞ እስኪገጣጠሙ ድረስ ከመጠበቅና ከመጠባበቅ ይልቅ፥ እስከዚያው ድረስ ሁሉም በየፈርጁ ብሔራዊ ግዴታውን ሊወጣ ይገባል፡፡ በዓለም ሕዝብ የትግል ታሪክ ሂደት፥ የነፃነትና የዴሞክራሲ ትግሎች ድል ሊጎናፀፉ የበቁት፥ የምሁሩን ድጋፍና ትብብር አግኝተው ነው፡፡ ሀገራችን አሁን ከደረሰችበት አሳዛኝና አደገኛ ሁኔታ አንፃር፥ ማንኛውም የኅብረተስብ ክፍል ተባብሮ ካልታገለ፥ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ትቆያለች ብሎ ተስፋ ማድረግ፥ ቢያንስ ሁኔታውን በቅጡ አለመገንዘብ ይሆናል፡፡*

*<u>ይህ መርኅ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን፥ ሀገርን ለማዳን በሚደረገው ብሄራዊ የነፃነት ትግል ሂደት፥ ሁሉም ዜጋ አጋ ሳይለይ፥ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም ማዕከል ባደረገ በሀገር አቀፍ ትግል መሳተፍና ብሔራዊ ጥሪንም በአስቸኳይ የመመለስ ግዴታ አለበት ፡፡ ዛሬ ቅድሚያ የሚሰጠው ምርጫ፥ ሁሉም ተባብሮ ሀገርን በጋራ የማዳን አጀንዳ ብቻ ነው፡፡ ሀገር ከተገኘ በኋላ ሌላው ምርጫ የሕዝብ ምርጫ ይሆናል፡፡</u>*

4) ከሁሉም በላይ የሆነውና የሁሉም ጉዳይ አጠቃላይ መደምደሚያ ሊሆን የሚገባው፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነትና የኢትዮጵያ ኀልውና ነው:: በመሆኑም፥ ዛሬ ከሁሉም በበለጠ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ያው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅምን ያስቀደመ ትግል ብቻ ይሆናል:: በዕርግጥም ኢትዮጵያን ማዳን አለብን ከተባለ፥ ከዚህ የበለጠና የተሻለ አማራጭ አይኖርም:: እንደማንኛቸውም የዓለም ሕዝቦች፥ እኛም ሠላምና ፀጥታ፥ ነፃነትና ዴሞክራሲ፥ ፍትኀ-ርትዕ፥ ልማትና ብልፅግና፥ ዕድገትና ሥልጣኔ፥ ፍስሀና ጤና እንፈልጋለን:: በዜጎቿ ዕኩልነት ላይ የተመሠረተ፥ አንድነቷ የተጠበቀና የዴሞክራሲ ሥርዓት የሰፈነባት ጠንካራ ሀገር እንፈልጋለን:: ከቅርብ ጎረቤቶቻችንም ይሁን ከሩቅ ወዳጆቻችን ጋር፥ በሰላም ተባብሮ መኖርን እንመኛለን:: ይህ ሁሉ ታላላቅና አግማሰ-ሰፊ የሆነ ዓላማና ምኞት የሚሳካው ግን አንድ ላይ ተባብሮ ሲሰሩና ሲታገሉ ብቻ ነው:: ዛሬ በዓለም ላይ ያሉ የበለፀጉ ሀገሮች አሁን ካሉበት ደረጃ ሊደርሱ የቻሉት፥ ተባብረውና ተዋኀደው በመሥራታቸው ነው:: ተቻችለውና ልዩነታቸውን አቀራርበው፥ <u>በልዩነት አንድነት</u> የሚለውን መርኀ አንግበው፥ ለአንድ ስትራተጂያዊ የሀገራቸው ጥቅም ብቻ ስለሚሰሩ ነው:: ይህንን መሠረታዊ ዕውነታ ማየት የኢትዮጵያ ሕዝብ በጉጉት ይመኛል:: ይፈልጋል::

የኢትዮያን ሕዝብ፥ በብሔር ከፋፍለው፥ በጎጥ ከልለው፥ በቋንቋ አለያይተው፥ በሃይማኖት አበጣብጠው ሀገሪቱን ለመበታተን ያደረጉት ሙከራ እስካሁን ጉዳት አላመጣም ብለን ራሳችንን ባናታልልም፥ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እስካሁን በእነርሱ አኩይ ወጥመድ አልገባላቸውም:: በዚህም ታላቅነቱን በድጋሜ አስመስክሯል:: ይህንን ታላቅነት ጠላት በአዳዲስ የተንኮል ዘዴ በበለጠ እንዳይፈታተነው ግን ከላይ በተራ ቁጥር 2፥ 3 እና 4 የተገለጹት ኃይሎች ማለትም፥ የተቃዋሚው ጎራ፥ የኢትዮጵያ ምሁራንና ምልአተ-ሕዝቡ በመተባበር፥ በተራ ቁጥር አንድ የተጠቀሰውን ቀንደኛ የኢትዮጵያ ጠላት ማለትም ወያኔን ተባብረው ማስወገድ ቀዳማይ የትግል አጀንዳቸው ሊያደርጉት ይገባል:: ይህንን አጀንዳ ለማሳካት ደግሞ፥ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም ማዕከል ያደረገ ትግል ተፋፍሞ መካሄድ አለበት::

ለጠላት መንበርከክ የሚሉት ቋንቋ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቋንቋ አይደለም! የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አቸናፊ ነው!!